## የመሰረታዊ አገልግሎት ማጭበርበሮችን መከላከል

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ አገልግሎት ኮሚሽን ለእርስዎ የቀረበ

## የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማጭበርበር

በሃገር አቀፍ ደረጃ ጉልህ የሆነ የመሰረተ ልማት ማጭበርበር የመጨመር ሁኔታ ተስተውሏል። የማጭበርበር ድርጊቱን የሚፈጽሙት አካላት ሸማቾች ገንዘባቸውን እና የግል መረጃቸውን አሳልፈው እንዲሰጧቸው በማድረግ ያታልሏቸዋል። ራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና ማሕበረሰብዎን እንዴት መከላከል እንዳለብዎ ይወቁ።

## ራስዎን ይከላከሉ

ልብ ይበሉ፤ እርስዎ አሳልፈው ካልሰጧቸው በስተቀር አጭበርባሪዎች ገንዘብዎን ወይም የግል መረጃዎን ሊያገኙ አይችሉም። ከእነዚህ የመሰረታዊ አገልግሎት ማጭበርበሮች ራስዎን ለመጠበቅ እነዚህን ጥቆማዎች ጥቅም ላይ ያውሉ፡-

- አጠራጣሪ ደዋዮች በሚሆኑበት ጊዜ ወዲያውኑ ስልክዎን ይዝጉና በቀጥታ ለመሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎ ይደውሉ
- የፋይናንስ መረጃዎች፣ የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥሮችን (social security number) ፣ የማለፊያ ቃላት (passwords) ወይም የልደት ቀንዎን ለሌላ አያጋሩ ወይም አያሳውቁ
- የእርስዎን ሒሳብ በሚመለከት ለሚኖሩ ማንኛውም ጥያቄዎች በቀጥታ ከመሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅትዎ ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ
- በስልክ ወይም በድረ-ገጻቸው አማካኝነት በቀጥታ ለመሰረታዊ አገልግሎት ኩባንያው ክፍያ ይፈጽሙ
- ያልታቀደ ጉብኝትን ለማረጋገጥ ለመሰረታዊ አገልግሎት ኩባንያው እስከሚደውሉ ድረስ ማንኛውም ሰው በቤትዎ ውስጥ እንዲገባ አይፍቀዱ።
- በአካባቢዎ አጭበርባሪዎች ያሉ ከሆነ ለፖሊስ እና ለጎረቤቶችዎ ያሳውቁ

የበለጠ ለማወቅ fightutilitiesscams.com